የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.8
ADDIS ABABA 15th February, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፹፱/፪ሺ፲፬

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ......................................ገጽ ፲፫ሺ፱፻፳፫

## Content

Regulation No. 489/2022

Public Service Transport Service Re-establishment Regulation ........Page 13923

## ደንብ ቁጥር ፬፻፹፱/፪ሺ፲፬

## የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፺፮ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፴፭(፫) እና ፵፯/፩/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፱/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## Regulation No. 489/2022

## PUBLIC SERVICE TRANSPORT SERVIC E RE-ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to the Article 96 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021 and Article 35(3) and 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as the "Public Service Transport Service Re-establishment Regulation No. 489/2022".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 29.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80001

Scanned by CamScanner

**፮. ዓላማ**

አገልግሎቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ከተጠቀሰው አገልግሎት በተጨማሪ ለሌሎች ተገልጋዮች በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፫/ ከዓላማው ጋር ተዛማጅ የሆኑ እና ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን፡፡

**፯. ስለ መፍረስ**

የሸበሌ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ፈርሶ በአገልግሎቱ ተጠቅልሏል፡፡

**፰. ካፒታል**

ለአገልግሎቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፭ ቢሊዮን (አምስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ ቢሊዮን ፰፻፮ ሚሊዮን ፭፻፷፫ሺ ፪፻፲፭ (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ አስራ አምስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

**፱. ኃላፊነት**

አገልግሎቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**6. Objectives**

The objectives for which the Service is established are:

1/ To provide transport service to public service employees during office opening and closing hours in Addis Ababa and peripheral cities to Addis Ababa;

2/ In addition to the services under Sub-Article (1) of this Article, to provide transport service to other users in Addis Ababa and Peripheral Cities to Addis Ababa;

3/ To engage in activities related to its objectives and other activities.

**7. Dissolution**

The Shebele Transport Share Company is hereby dissolved and acquired by the Service.

**8. Capital**

The authorized capital of the Service is Birr 5,000,000,000 (Five Billion Birr) of which 1,806,563,215 (One Billion Eight Hundred Six Million Five Hundred Sixty Three Thousand Two Hundred Fifteen Birr) is paid up in cash and in kind.

**9. Liability**

The Service may not be held liable beyond its total assets.

Scanned by CamScanner

**፲. <u>አገልግሎቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

አገልግሎቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

**፲፩. <u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

፩/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፺፬ የተቋቋመውና በፕራይቬታይዜሽን አዋጅ ቁጥር ፻፵፮/፲፱፻፺፱ መሠረት ወደ አክሲዮን ማሕበርነት የተለወጠው የሸበሌ ትራንስፖርት አክሲዮን ማሕበር መብቶችና ግዴታዎች ለአገልግሎቱ ተላልፈዋል፡፡

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፲፫ የተቋቋመው የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለተቋቋመው አገልግሎት ተላልፈዋል፡፡

**፲፪. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፲፫፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (እንደተሻሻለው) ቁጥር ፫፻፷፪/፪ሺ፲፭ እና የሸበሌ ትራንስፖርት አክሲዮን ማሕበር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፺፬ ተሽረው በዚህ ደንብ ተተክተዋል፡፡

**10. <u>Duration</u>**

The Service is established for an indefinite period.

**11. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

1/ The rights and obligations of Shebele Transport established through the Council of Ministers Regulation No. 192/1994 and reorganized as Share Company through Privatization of Public Enterprises Proclamation No. 146/1999 are hereby transferred to the Service.

2/ The rights and obligations of Public Service Employees' Transport Service Enterprise established in accordance with Council of Ministers Regulation No. 298/2013 are hereby transferred to the Service.

**12. <u>Repealed Laws</u>**

The Public Service Employees' Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 298/2013; the Public Service Employees' Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation (as amended) No. 362/2015 and Shebele Transport Establishment Council of Ministers Regulation No. 192/1994 are hereby repealed and replaced by this Regulation.

Scanned by CamScanner

**፲፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**13. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 15th Day of February, 2022**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned by CamScanner